የአሌ ቋንቋ ሥርዓተ ድምጽና ሥርዓተ ጽሕፈት

ዮናስ በቀለ[1] እና ሀረገወይን ከበደ[2]

አሕጽሮተ ጥናት

ይህ ጥናት በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የሚነገረውና የኩሺቲክ ቋንቋ ቤተሰብ አባል የሆነው የአሌ ቋንቋን የድምፅ ሥርዓት መመርመር እና ለቋንቋው ተስማሚ የሆነ ሥርዓተ ጽሕፈት መቅረጽ ላይ ትኩረቱን አድርጓል። ጥናቱ በቋንቋው ውስጥ ያሉትን ተነባቢ ድምፆችንና አናባቢ ድምፆችን ጨምሮ የቋንቋዉን ባሕሪ እና የድምፅ ቆጠራ አጠቃላይ መግለጫ ለመስጠት ያለመ ነው። በተጨማሪም እነዚህን ድምፆች ለመወከል የሚያገለግሉትን የአጻጻፍ ሥርዓት ስምምነቶችን ጥናቱ አቅርቧል። በድምጽ ሥርዓቱ እና ሥርዓተ ጽሕፈት መካከል ያለውን ግንኙነት መርምሯል። መረጃ የተሰበሰበው የስዋዴሽ የቃላት ዝርዝር በመጠቀም በቃለ መጠይቅ፣ በጽሑፍ መጠይቅ እና በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተናጋሪዎች ምልከታ ነው። ትንታኔው የሚያተኩረው የአሌ ስነ-ድምጽና ስርዓተ-ድምጽ አሐዶችን በመለየት እንዲሁም ውክልናቸውን የሚቆጣጠሩትን የአጻጻፍ መርሆችን በመመርመር ላይ ትኩረት አድርጓል። የጥናቱ ግኝቶች ስለአሌ ቋንቋ ጠለቅ ያለ ግንዛቤ ከመስጠቱም ባሻገር ለወደፊት ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ምርምር ማድረግ ለሚፈልጉ ምሁራን ሁሉ ጠቃሚ መረጃ ይሰጣቸዋል ተብሎ ይታመናል። እንዲሁም የቋንቋው ተናጋሪ የሆነው የአሌ ሕዝብን ለማስተዋወቅ ተጨማሪ መረጃ እና ግንዛቤ እንዲፈጠር አስተዋጽኦ ያደርጋል። ጥናቱ የአሌ ቋንቋ የድምፅ ሥርዓቱ ዝርዝር መግለጫ በመስጠት 32 ተነባቢ ድምፆች እና አምስት አናባቢ ድምፆች ጥናቱ ለይቷል። የተነባቢ ድምፆች መጥበቅና መላላት የትርጉም ለውጥ እንደሚያመጡና እንደዚሁ የአናባቢዎች መርዘምና ማጠር የትርጉም ለውጥ እንደሚያመጡ በጥናቱ ተመላክቷል። በመጨረሻም፣ የተሻለ አገልግሎት ሊሰጥ የሚችለውን ሥርዓተ ጽሕፈት ለቋንቋው ተዘጋጅቷል።

ቁልፍ ቃላት፡ [የአሌ ቋንቋ፣ ሥርዓተ ድምፅ፣ ሥርዓተ ጽሕፈት፣ አሌ ዞን፣ ደቡብ ኢትዮጵያ]

[1] አቶ ዮናስ በቀለ በአዲስ አበባ ዩኒቨሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች ማእከል ተማራማሪ ነው።

[2] ሀረገወይን ከበደ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቀድሞ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ በልደርባ የነበሩ

1. *ዳራ*

ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በሀገሪቱ ከሚገኙ ክልሎች አንዱና ብዙ ብሔረሰቦች የሚኖሩበት ክልል ነው። በክልሉ ከሚኖሩ ብሔረሰቦች ውስጥ አንዱ የአሌ ብሔረሰብ ነው። አሌ ከዚህ ቀደም ገዋዳ ተብሎ ይጠራል። በዚሁ ብሔረሰብ ላይ ጥናት ያካሄዱ ምሁራን ገዋዳ የሚለውን ስም በመጠቀም ነው ጥናታቸውን ያደረጉት። ከእነዚህ ምሁራን መካከል (Haregewoin 2003) ፣ (Geberew 2003) ፣ (Firew 2011) እና (Assefa 2010) ይገኙባቸዋል። ይሁንና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሕዝቡ ስሙን ወደ አሌ ቀይሮት ይሄው ስም አሁን አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። የአሌ ብሔረሰብ ቋንቋ እንደ ብሔረሰቡ አጠራር “ፓኮ አሌ” በመባል የሚጠራ ሲሆን በአማርኛ የአሌ ቋንቋ እንደማለት ነው።

የአስተዳደር መዋቅር በምናይበት ጊዜ አሌ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ከሚገኙት ዞኖች አንዱ ነው። በአሌ ዞን አንድ የከተማ አስተዳደር እና አንድ የወረዳ የአስተዳደር መዋቅሮች ይገኛል። እነዚህም ኀላንጎ ከተማ አስተዳደር እና ኀላንጎ ዙሪያ ወረዳ ናቸው። እንዲሁም በአሌ ዞን ባጠቃላይ ከወረዳ በታች ያሉት የአስተዳደር መዋቅሮችን ስንመለከት 18 የቀበሌ የአስተዳደር መዋቅሮች ይገኛሉ። እነዚህም ገዋዳ ከተማ፣ ገዋዳ ገጠር፣ ኢያና፣ ቃርቃርቴ፣ ጋርጋማ፣ ቱሩባ፣ ጉማ፣ ኀላንጎ፣ ዲክንቲ፣ ላልቾ፣ ጎሮዜ፣ ደልበና ጋማ፣ ደጋ ማሽሌ፣ አዲስ ኦልትማ፣ ቦሌ፣ ፀማሀ፣ ሎክቴና ዱጉማ ናቸው።

Firew (2011) እና Black (1976፤222) እንደጻፉት ከሆነ ገዋዳ (አሌ) በኢትዮጵያ ውስጥ አነስተኛ ቁጥር ካላቸው ብሄረሰቦች አንዱ ሲሆን የሚገኘውም በኦሞ ወንዝ አካባቢ ከጫሞ ሀይቅ በስተ ምዕራብ እና በሰሜን ምሥራቅ በኩል ደግሞ ከኮንሶ ይዋሰናል። Geberew (2003፣ Bender (1971፡187 እና 1976፡8)፣ እንደጻፉት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ከሚነገሩ እና ብዙም ካልታወቁት የምስራቅ ኩሺቲክ ቋንቋዎች መካከል ጋዋዳ አንዱ እንደሆነ ነው። በ2007 በተደረገው የኢትዮጵያ ህዝብና ቤቶች ቆጠራ መሠረት በኮንሶ እና በደራሼ ወረዳዎች 68,000 ገዋዳዎች አሉ (Firew 2011፡1)። ገዋዳ (አሌ) በሰሜን ማሌ፣ በምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ ፀማይ፣ በደቡብ ቦረና-አርሲ-ጉጂ ኦሮሞ፣ በደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ ኮንሶ፣ በሰሜን እና ሰሜን ምስራቅ ደራሼ፣ በስተሰሜን ደግሞ ከቡሳ ጋር ይዋሰናል (Assefa 2010፡1) ።

የቋንቋን የድምፅ ሥርዓት መረዳት በጣም አስፈላጊና ቁልፍ ጉዳይ ነው። የአንድ ቋንቋ የድምፅ ሥርዓት በመጀመሪያ፣ በዚያ ቋንቋ ውስጥ ቃላት እንዴት እንደሚፈጠሩ ያሳያል። በሁለተኛ ደረጃ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተናጋሪዎች በንግግራቸው የሚያካትቷቸውን ድምጾች እንዴት እንደሚገነዘቡ እና እንደሚፈጥሯቸው ግንዛቤን ይሰጣል። በመጨረሻም፣ ይህ እውቀት የቋንቋውን ቃላት ትክክለኛ አጠራር ያመቻቻል (Crystal, 2008፣ 264-265) ። ስለዚህ የአንድ ቋንቋ የድምጽ ሥርዓት የተለያዩ ቃላትን እንድንለይ፣ የቃላትን ትርጉም እንድንረዳና ስሜትን እንድንገልጽ ስለሚያስችለን ለቋንቋው ለራሱ አስፈላጊ አካል ነው።

ሥርዓተ ጽሕፈት በጽሑፍ ቋንቋን ለመወከል የሚያገለግል የፊደላት እና ምልክቶች ሥርዓት ነው። ይህ በጣም አስፈላጊ ነው ምክንያቱም አፋቸውን በቋንቋው የፈቱ ተናጋሪዎች ግንኙነትን ለማጎልበት የሚጠቀሙባቸውን ደረጃቸውን የጠበቁ የአጻጻፍ ሥርዓቶችን ስለሚያስችላቸው፣ እንዲሁም አፋቸውን በቋንቋው ያልፈቱ ተናጋሪዎች ሌላ ቋንቋ እንዲያጠኑ እና የጽሑፍ ቅጹን እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ እንዲማሩ መንገድ ስለሚከፍትላቸው ነው። በአጠቃላይ፣ ሥርዓተ ጽሕፈት ለየማንኛውም ቋንቋ አስፈላጊ ነው። የቋንቋን ድምፅ በጽሑፍ የሚወክልበትን መንገድ ያቀርባል፣ ይህም ተግባቦትን ለማመቻቸት እና ቋንቋን ለመጠበቅ ይረዳል።

2. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋንኛ ዓላማ ለአሌ ማኅበረሰብ ተቀባይነት ያለውና ለቋንቋው ተስማሚ የሆነ ንጥረ ድምፆችን በአግባቡ የሚወክል ሥርዓተ ጽሕፈት ማዘጋጀት ነው። ዝርዝር ዓላማዎች አድርጎ ጥናቱ የተነሳው ደግሞ፡

2..1 የአሌን ማህበረሰብ ማስተዋወቅ፣

2.2. ቋንቋው ሥርዓተ ጽሕፈት ለማዘጋጀት መሠረታዊ እና እጅግ ጠቃሚ የሆነውን የቋንቋውን ንጥረ ድምፅ መለየትና የድምፀ ልሳናዊ ገለጻ ማከናወን፣

2.3 ለቋንቋው ቅቡልና ተስማሚ ሥርዓተ ጽሕፈት ማዘጋጀት፣ የፊደል ገበታ ማዘጋጀት እንዲሁም ሥርዓተነጥብ ምልክቶች ማዘጋጀት ናቸው።

3. የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት በዋናነት የአሌ ቋንቋን የድምፅ ሥርዓት ለማጥናትና ለቋንቋው ተስማሚ የሆነ ሥርዓተ ጽሕፈት ለማዘጋጀት የተካሄደ ነው። የጥናቱ ዘዴ በሚከተሉት ዋና ዋና እርከኖች የተዋቀረ ሲሆን፣ በእያንዳንዱ እርከን የቋንቋው ተናጋሪዎች ጋር በቅርበት በመሥራት ተከናውኗል።

1. የመረጃ አሰባሰብ

የጥናቱ መሠረታዊ መረጃ በቀጥታ ከማኅበረሰቡ መካከል በመገኘት በሚከተሉት ዘዴዎች ተሰብስቧል። መስክ ምርምር (Fieldwork)፣ ጥናቱ በአሌ ዞን ውስጥ በአካል በመገኘት የቋንቋውን ተፈጥሯዊ አካባቢ በመጠቀም ተከናውኗል። የቃላት ዝርዝር (Swadesh Wordlist) ፣ የጥናቱ ዋነኛ መሳሪያ የሆነው የ400 ቃላት የ (Swadesh wordlist) ዝርዝር በመጠቀም መሠረታዊ ቃላት ተሰብስበዋል። ይህም መሠረታዊ ንጥረ ድምፆች (phonemes) ለይቶ የማወቅ ሂደትን ቀላል አድርጎታል። በተለያዩ የዕድሜ ደረጃ ላይ የሚገኙ 10 በአፍ መፍቻነት ቋንቋውን የሚናገሩ የተሻለ ልምድና ብቃት ያላቸው የመረጃ ሰጪዎቸን፣ ከእነዚህም 4ቱ ሴቶች የሆኑትን በመጠቀም መረጃዎች ተሰብስበዋል።

ቃለ-መጠይቅ (Interviews)፣ ከቋንቋው ተናጋሪ የማህበረሰብ አባላት ጋር ቃለ-መጠይቆች እና ቃለ-ምልልሶች ተካሄደዋል። ከላይ የተጠቀሱት መረጃ ሰጪዎች እድሜያቸው ከ20-60 ክልል

ውስጥ የሚገኙ ናቸው። በተለይም ተመሳሳይ ቃላትን የሚለይ የድምፅ አሃዞችን (minimal pairs) ለማግኘት ይህ ዘዴ ወሳኝ ሚና ተጫውቷል።

የተፈጥሯዊ ንግግር መዝገብ (Recording of Natural Speech): ታሪኮች፣ ውይይቶች እና የዕለት ተዕለት ንግግሮች በጥራት ያለው የድምፅ መቅረጫ መሣሪያ ተመዝግበዋል። ይህም ድምፆች በተለያዩ የንግግር አገባጠሞች ውስጥ እንዴት እንደሚገኙ ለመተንተን አስተዋጽኦ አድርጓል። በተጨማሪም ተመራማሪዎቹ በማኅበረሰቡ ውስጥ በተገኙበት ጊዜያት ሁሉ የቋንቋውን ተፈጥሯዊ አጠራርና አጠቃቀም ለማስተዋል ችለዋል።

2. **የመረጃ ትንተና ዘዴዎች** (Data Analysis Methods)

የተሰበሰቡት መረጃዎች በስነ-ቋንቋ ትንተና ዘዴዎች መሰረት ተተንትነዋል። በዚሁ መሰረት በቋንቋው ውስጥ የሚገኙ ተነባቢ ድምጾችና አናባቢ ድምጾች ተለይተው ቀርበዋል። በተካሄደው የንጥረ ድምፆች ትንተና እና ልየታ መሰረት በአሌ 32 ተነባቢ እና 5 አናባቢ ድምፆችን ጥናቱ ለይቶ አቅርቧል።

3. **የሥርዓተ ጽሕፈት ንድፍ ሂደት** (Orthography Design Process)

የቋንቋውን ስነ-ድምፅ መሠረት በማድረግ የጽሕፈት ሥርዓቱ በሚከተሉት ንድፍ መርሆዎች ተዘጋጅቷል (Cahill & Karan, 2008) ። ፎኔሚክ መርህ (Phonemic Principle): አንድ ፎኒም በአንድ ፊደል (ወይም ፊደላት ጥምር) ይወከላል። ለምሳሌ፣ /tʃ/ በ <c'> ሲወከል፣ /ɲ/ በ <ny> ተወክሏል።

ተግባራዊነትና ተቀባይነትን (Usability and Acceptability) በተመለከተ ፊደላቱ በቋንቋው ተናጋሪዎች ለመጠቀም ቀላል እንዲሆኑ ታስቧል። ይህም በአማርኛ/ኦሮምኛ ተማሪዎች የሚታወቁ የላቲን ፊደላትን መሠረት በማድረግ ተግባራዊ ሆኗል። ለአዳዲስ ድምፆች (እንደ /ɓ, ɗ, ʕ, ħ/) የተለዩ ነገር ግን ከዋናው ፊደል ጋር የሚዛመዱ ምልክቶች (እንደ bh, dh, qh) ተመርጠዋል።

ሙከራ (Pilot Testing): የተዘጋጀው ፊደል ገበታና የጽሕፈት ሕጎች በአጭሩ የተጻፈ ጽሑፍ (የቀረበው አጭር ታሪክ) በመጠቀም ተሞክሯል። በዚህም የተቀረጸው ሥርዓተ ጽሕፈት ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል ለማረጋገጥ ተችሏል።

4. **የምርምር ስነ-ምግባርን በተመለከተ** (Research Ethics)

ጥናቱ በሚከተሉት መርሆዎች መሠረት ተካሂዷል፡-

የመረጃ ሰጪዎች ፈቃድን (Informed Consent) አስመልክቶ መረጃ የሰጡ ሁሉ መረጃ ከመስጠታቸው በፊት የጥናቱ ዓላማ በሙሉ ተገልጾላቸዋል። በዚሁ መሰረት ፈቃደኝነታቸው ተረጋግጧል። የማኅበረሰብ ተሳትፎ (Community Participation) አስመልክቶ የጽሕፈት ሥርዓቱን በማዘጋጀት ሂደት የቋንቋው ተናጋሪዎች እና የማኅበረሰቡ አባላት የተሳተፉ ሲሆን፣ የተዘጋጀውም ሥርዓት ጽሕፈት በማኅበረሰቡ ተቀባይነት ያለው መሆኑ ተረጋግጧል።

4. የአሌ ሥርዓተ ድምፅ

ይህ ጥናት ከተለያዩ ጥናቶች ጋር ሲነፃፀር (Black, 1976; Haregewoin ፣ 2003; Gebrew፣ 2003; Firew፣ 2011; Assefa፣ 2010) ተጨማሪ ንጥረ ድምፆች ተገኝተዋል። በዚሁ መሰረት በቋንቋው ላይ የስነልሳን ጥናት ያካሄዱ የስነ ልሳን ተመራማሪዎች በቋንቋው ውስጥ የሚገኙት ድምፆችን አስመልክቶ የተለያየ ቁጥር ሰጥተዋል። ለምሳሌ Black (1976፡224) እና Geberew (2003) አሌ 25 ተነባቢዎችና አምስት አናባቢዎች አሉት ሲሉ ጽፈዋል። Black (1976: 224) የላንቃ ሰርናዊ [ɲ] እና የጉርአዊ (a pharyngeal fricative) [ħ] ድምጾቻ አሉ ሲል እነዚህ ድምፆች በሀረገወይን (2003፡42-56) ጥናት ውስጥ አልተካተቱም። በእሷ ጥናት የተገኙት 26 ተናባቢዎች እና 5 አናባቢዎች ብቻ ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ ገበረው (voiced implosives) /ɓ/, / ɗ/እና /ɠ/, ጉርአዊ (the voiceless pharyngeal)/ħ/ እንዲሁም እንጥላዊ (the voiceless uvular) /χ/ ድምፆችን በጥናቱ ግኝት ውስጥ አላካተተም። Horsch, (2006) ለዱላይ ቋንቋዎች ስብስብ የሥርዓተ ጽሕፈት ሀሳብ ባቀረበበት ጥናቱ ውስጥ 29 ተነባቢዎችንና 5 አናባቢዎችን ከሌሎች የጉርአዊነት (pharyngealized) አናባቢዎቻቸው ጋር በጥናቱ አመላክቶ እናገኛለን።

ይሁንና ይህ ጥናት ከላይ ያየናቸውና በቋንቋው ላይ በተለያየ ጊዜ ጥናት አካሂደው አንዱ አግኝቶ ሌላው ያላገኟቸው ድምጾችን በሙሉ ሊያገኛቸው ችሏል። በሀረገወይን ጥናት ውስጥ ያልተካተቱት ለምሳሌ [ɲ] እና የጉርአዊ (pharyngeal fricative) [ħ] በዚህ ጥናት ተገኝተዋል። ለምሳሌ [ɲ] ን ስንመለከት ɲari 'አስፈራራ'፣ ɲaaɲa 'ቲማቲም'፣ ɲuɠe 'ጨቅላ' በሚሉ ቃላት የድምጹ መኖር ተረጋግጧል። እንደዚሁ [ħ]ን ደግሞ ħanɗurte 'እትብት'፣ salaħ 'አራት' በሚሉ ምሳሌዎች ማረጋገጥ ተችሏል። በተመሳሳይ መልኩ ገብረው ያላገኛቸው ድምጾች /ɓ/፣ /ɗ/፣ /ɠ/ እና /χ/ ሲሆኑ በዚህ ጥናት እነዚህ ድምጾች ሊገኙ ችለዋል። ለምሳሌ፣ /ɓ/ ɓati 'ለካ' iɓːe 'ፍሬ' saɓi 'አቦካ' ድምጹ እንዳለ ያሳያል። /ɗ/ ድምጽን በምንመለከትበት ጊዜ ɗipa 'መቶ' maːɗe 'ጥሬ' ɗuːtːako 'ቁልቁለት' በሚሉ ቃላት ድምጹ መኖሩን ማረጋገጥ ችለናል። እንደዚሁ /χ/ን ስናይ maχːe 'እቃ' χoχno 'ጉድጓድ' aːχe 'ቅጠል' በሚሉ ምሳሌዎች የድምጹ መኖር በጥናቱ ተረጋግጧል።

በመሆኑም ከላይ የተመለከቱትን በተለያዩ ጊዜያት የተደረጉ የጥናት ውጤቶችን ከመረመርንና አዲስ ከተሰበሰበው የቋንቋው መረጃ ጋር ካነፃፀርናቸው በኋላ በአሌ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙት ድምፆች 32 ተናባቢዎች እና 5 አናባቢዎች ናቸው ከሚል መደምደሚያ ላይ ደርሰናል። በተጨማሪም የአናባቢዎች መርዘም ወይም ማጠር እና የተናባቢዎች መጥበቅ ወይም መላላት በቃላት መካከል የትርጉም ልዩነት የሚያመጣ መሆኑን ከዚህ ጥናት ለመረዳት ችለናል። የዚህ ጥናት የተገኙት ድምጾች እንደሚከተለው በተነባቢ እና በአናባቢ ሠንጠረዦች ቀርበዋል።

4.1 የአሌ ተነባቢ ድምፆች በአይፒኤ (Consonant Phonemes in IPA)

	Bilabials ከንፈራዊ	Labiodentals ከንፈር ወስናዊ	Alveolars ድዳዊ	Palatals ላንቃዊ	Velars ትናጋዊ	Uvulars እንጥላዊ	Pharyngeals ጉርአዊ	Glottals ማንቁርታዊ
እግድ (Plosives ነዛሪ (Vd)	b		d		g			ʔ
ኢነዛሪ (Vl)	p		t		k			
ፈንጅ (Implosives)	ɓ		ɗ		ɠ	ʛ		
ፈንጂ (Ejective)			t̓	tʃ'	k̓			
ሹልክልክ (Fricatives)		f	s z	ʃ	x	χ	ħ ʕ	h
ፈንጅ (Ejective)			s'					
ፍትግ (Affricatives)				tʃ				
ሰርናዊ (Nasals)	m		n	ɲ				
ጎናዊ (Lateral)			l					
ላሽ (Flap)			r					
ከፊል አናባቢ (Glides)	w			j				

ሠንጠረዠ 1 የአሌ ተነባቢ ድምፆች በአይፒኤ

ከዚህ ቀጥሎ የእያንዳንዱ ደምጽ ስርጭት እንደሚከተለው ቀርቧል።

/p/ Voiceless bilabial plosive

piʔ:at:e ልጅ ፍየል por tʃo ገብስ irpante መንጋ gaspo ስንዴ tap:i ስድስት

/b/ voiced alveolar plosive

nabse ሕይወት ʕarabgo ዝሆን tibo ተበተበ ħat'umbe መጥረጊያ

/d/ voiced alveolar plosive

dilango ቂጣ adungo ጡት ande ውሀ

/ɓ/ ነዛሪ የከንፈር ፈንጅ

ɓati ለካ **iɓːe** ፍሬ **saɓi** አቦካ **ɓeɠ i** ገደላቸው **tuɓa** ውቀጡ **tuɓ** ውቀጥ!

/m/ Voiced bilabial nasal

muʃːo ቁርስ **imːaje** ቀበሩ **orħami** ተዋጋ **tuːma** ነጭ ሽንኩርት **ħaːm** ንቀል!

/w/ Voiced bilabial glide

wale ቆንጨራ **wawe** ምራቅ **hawle** መቃብር **kar:awo** ፌንጣ **taw:o** እባብ

/f/ Voiceless labio-dental fricative

foħo ሽለቆ **piːfe** ምሳ **tafo** ጭን/ታፋ **ʔafte** መኝታ **saffa** ዳሀ !

/t/ Voiceless alveolar plosive

tiʃe እሸት **ɗoti** ወጋ **salete** አዋጅ መንገር **qayt:o** ዓርብ **sit** ጥለፍ!

/t̓/ Voiceless alveolar ejective

t̓ihile ክንድ **t'eʔajo** ትንሽ ፌንጣ **jeħet'ːi** አስቀያሚ **ħat'umbe** መጥረጊያ **ɠut̓** በጥስ(ጧ አድርገህ)!

/ɗ/ Voiced alveolar implosive

ɗipa ሙቶ **ma:ɗe** ጥሬ **ɗu:t:ako** ቁልቁለት **iɗ:a** ቀይ **ɠut'aɗi** ወሰነ

/k/ Voiceless velar plosive

kolan ዘጠኝ **kere** መቀመጫ አይነት **luk:alak:o** አውራ ዶሮ **lak:i** ሁለት **rak** አንጠልጥላቸው!

/k'/ Voiceless velar ejective

K'ark'ar:o እርዳታ **hek'uri** ራሱን ጣለ **ik'aɠi** ተፀዳዳ **hok'aba** እርጥብ **hak'i** ብጣ!

/g/ Voiced velar plosive

patango ጠባሳ **tʃigno** ፍቅር **girtʃa** የጆሮ ጉትቻ

/ɠ/ Voiced velar implosive

ɠubo ተራራ **hoɠo** ሽፍታ **aɠa** አለ **oɠːa** **ɗːi** ረገጠ **liɠ** ውጣ !

/n/ Voiced alveolar nasal

neħte ሴት(ለእንስሳ) **awne** ምሽት **patango** ጠባሳ **man:e** ቤት **ʧun** ላጭ!

/**ɲ**/ Voiced palatal nasal

ɲari አስፈራራ **ɲaɲa** ቲማቲም **maɲri** ረከሰ **ɲuɠe** ጨቅላ

/**l**/ Voiced alveolar lateral

Le:me ቋቁ ቻ **maltolakːo** ራሰ በራ **luk:ale** ዶሮ **sutalo** ተባይ **fil** አበጥር(ፀጉር) !

/**r**/ Voiced alveolar trill

raʔ:o ቀይ ጉንዳን **orːe** ሸከላ ሰሪ **karko** እንጨት **ature** ድመት **sorː** ሩጥ !

/**j**/ Voiced palatal glide

hejho ምግብ **isɠaje** ቅማል **imːaji** ቀበረ **paj** በል !

/**tʃ'**/ Voiceless palatal plosive

tʃ'igno ፍቅር **ɠantʃari** ፊቱን አኮማተረ **kaːtʃ'e** ጤፍ **girtʃ'a** የጆሮ ጉትቻ **tʃ'eɠte** ደም

/**χ**/ ኢነዛሪ የእንጥል ሽሉክሉክ

Xaf:i መጣ **χasoɗi** ደስ አለው **ma χ:e** እቃ **χoχno** ጉድጓድ **a: χe** ቅጠል

/**x**/ Voiceless velar fricative

xai ተነሳ **ɠjxo** ሰው

/**z**/ voiced alveolar fricative

zija ጀግና **izeh** ሦስት

/**ɠ**/ Voiced uvular implosive

ɠ u ɠ ጠምዝዝ ! **soɓor ɠ o** ትል **is ɠ aje** ቅማል **ɠ o ɠ e** ቅርፊት **saq** ! እረድ!

/**ʔ**/ Voiced glottal plosive

ɓoʔi ፊነዳ **ʔeme** በግ **kerʔko** ሌባ **raʔ** ተኩስ!

/**s**/ Voiceless alveolar fricative

salaħ አራት **soak:o** ጠንቋይ **hosibletuba** ቀጥቃጭ **ise** እሷ **las:** ሽጥ!

/s'/ voiceless alveolar ejective
kas'o ፀጉር

/ʃ/ Voiceless palatal fricative
ʃap: ane ቋጠሮ **kiʃno** ብዛት **ʃel:ate** ከሀዲ/ ዘራፊ **muʃ:o** ቁርስ **χaʃ** ጥሪብ/ቅርጽ አውጣ!

/t ʃ/ Voiceless palatal plosive
tʃele ካብ **tʃaħan** ሰባት **hejhitʃo** እንግዳ **arabatʃe** ጅብ

/ħ/ Voiceless pharyngeal fricative
ħanɗurte እትብት tʃaħan ሰባት **salaħ** አራት

/ʕ/ voiced pharyngeal fricative
ʕarabgo ዝሆን **puk:ʕate** ራስ **karʕito** ሆድ

/h/ Voiceless glottal fricative
hawle መቃብር huiɗ:a ቀዩ tahan ሰባት **hoɗam:a ታላቅ hermale የሜዳ አህያ**

4.2 አናባቢዎች (Vowels)
አሌ እንደአብዛኞቹ የኩሽ ቋንቋዎች የሚከተሉት 5 አናባቢዎች አሉት፡፡

የአሌ የአናባቢ ድምፆች ስርአት (Vowels system of Ale)

	Front	Central	Back
Close	i [i]		u [u]
Mide	[e]		o [o]
Open		a [ɑ]	

4.2 ቀለም

በፎኖታክቲክስ ትንተና (Phonotactic Analysis) የቀለም አወቃቀር (syllable structures) እና በቋንቋው ውስጥ የሚፈቀዱ የድምጽ ቅንጅቶች (sound combinations) ተለይተዋል፡፡ የተነባቢ ድምፆች ጥብቀት (gemination) እና የአናባቢዎች ርዝመት (vowel length) የትርጉም ለውጥ እንደሚያመጣ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ የቀለም ዓይነቶችን (Syllable Types) በተመለከተ አሌ

ስምንት መሠረታዊ የቀለም ዓይነቶች አሉት። እነዚህም V, VV, VC, CV, CVV, CVC, VVC, እና CVVC (ፍሬው፣ 2011፣ ገጽ 50፣ ገብረው፣ 2003 ገጽ 10-11)።

የቀለም አቀማመጥ (Syllable Template) ሲታይም ቋንቋው የሚከተለው አጠቃላይ የቀለም አቀማመጥ አለው። (C) V_1 (V_2) (C) ይህም ማለት መነሻ (onset) እና መድረሻ (coda) ሲሆኑ፣ ዋና (nucleus) ደግሞ የግድ መኖር ያለበት ነው። ሁለት የተለያዩ አናባቢዎች በተከታታይነት መገኘት የቋንቋው ሥርዓት አይፈቅድም (ፍሬው፣ 2011፣ ገጽ 72፣ገብረው፣ 2003 ገጽ 10-11)) ።

እንደዚሁም የድምፅ ቅደም ተከተል ገደቦችን (Phonotactic Constraints) በተመለከተ ሁለት አናባቢ ድምፆች በማንኛውም ቃል መጀመሪያ (word-initial) ወይም መጨረሻ (word-final) ላይ አንድ ላይ ሊገኙ አይችሉም። የሦስት ተነባቢ ድምፆች (tri-consonant clusters) በማንኛውም ቦታ ተከታትሎ መምጣት የቋንቋው ሥርዓት አይፈቅድም።

ሁለት ተነባቢ ድምፆች የሚፈቀዱት በቃል መካከል (word-medial) ብቻ ነው። (ፍሬው፣ 2011፣ ገጽ 97 ገብረው፣ 2003 ገጽ 10-11) ።

የቀለም ክብደት (Syllable Weight): በሞራይክ ሞዴል መሠረት ቀላል የቀለሞች (ምሳሌ፡ CV) አንድ ሞራ (monomoraic) ሲሆኑ፣ ከባድ የቀለሞች (ምሳሌ፡ CVC, CVV) ሁለት ሞራ (bimoraic) ይይዛሉ። ሲላብሎች ከሁለት በላይ ሞራ ሲይዙ (ምሳሌ፡ CVVC እንደ /soor/ 'ኍጫ') "በጣም ከባድ" (super heavy)" ይባላሉ (ፍሬው፣ 2011፣ ገጽ 89) ።

በአሌ ቋንቋ ከፍተኛው የቀለም መዋቅር እንደሚከተለው ነው።



5. የአሌ ሥርዐተ ጽሕፈት (The orthography)

5.1 የተነባቢ ድምፆች ውክልና

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው በተደረገው የስነ ድምፅ ፍተሻ መሠረት በአሌ ቋንቋ ውስጥ 32 ተነባቢ ድምፆችን መለየት ተችሏል። እነዚህ ተነባቢ ድምፆችን በሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን። በመጀመሪያው ክፍል ከእንግሊዘኛ ቋንቋ ተነባቢዎች ጋር ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ንበት ያላቸውና በእንግሊዘኛው ፊደላት ምልክቶች ሊወከሉ የሚችሉ ሲሆኑ የቀሩት ደግሞ በአሌ ቋንቋ ውስጥ ብቻ የሚገኙና በእንግሊዘኛ ፊደላት ሊወከሉ የማይችሉ ድምፆች ናቸው።

ከእንግሊዘኛ ድምፆች ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው የአሌ ድምፆች በሚከተለው ሠንጠረዥ ውስጥ በተቀመጡት መልክ በእንግሊዘኛ ፊደላት ተወክለው ቀርበዋል።

Phonemes in IPA symbols	Phones	Graphemes
/p/ Voiceless bilabial plosive	[p]	<p>
/b/ Voiced bilabial plosive	[b]	<b>
/d/ voiced alveolar plosive	[d]	<d>
/m/ Voiced bilabial nasal	[m]	<m>
/f/ Voiceless labio-dental fricative	[f]	<f>
/t/ Voiceless alveolar plosive	[t]	<t>
/tʃ/ Voiceless palatal plosive	[tʃ]	<ch>
/s/ Voiceless alveolar fricative	[s]	<s>
/z/ voiced alveolar fricative	[z]	<z>
/s'/ voiceless alveolar ejective	[s']	<s'>
/ʃ/ Voiceless palatal fricative	[ʃ]	<sh>
/k/ Voiceless velar plosive	[k]	<k>
/g/ Voiced velar	[g]	<g>

plosive		
/n/ Voiced alveolar nasal	[n]	<n>
/l/ Voiced alveolar lateral	[l]	<l>
/r/ Voiced alveolar trill	[r]	<r>
/w/ Voiced bilabial glide	[w]	<w>
/j/ Voiced palatal glide	[j]	<y>
/h/ Voiceless glottal fricative	[h]	<h>

ሠንጠረዥ 2 የአሌ ተነባቢ ድምፆች ውክልና

በሁለተኛው ክፍል የሚመደቡት በአሌ ብቻ የሚገኙና በእንግሊዘኛ ቋንቋ የሌሉ ድምፆች አዳዲስ ወካይ ምልክቶች ያስፈልጋቸዋል። በመሆኑም እነዚህ ድምፆች በሚከተለው መንገድ የፊደል ውክልና እንዲኖራቸው ተደርጓል።

ንጥረ ድምፆች በአይፒኤ Phonemes in IPA symbols	ድምጹ Phones	የተወከለው ፊደል Graphemes
/t' / ኢነዛሪ የድድ ፈንጅ (Voiceless alveolar ejective)	[t̓]	<t'>
/k' / ኢነዛሪ የትናጋ ፈንጅ (Voiceless velar ejective)	[k̓]	<k'>
/tʃ/ ኢነዛሪ የላንቃ ፍትግ (Voiceless palatal affricate)	[tʃ]	<c'>
/ɲ/ ነዛሪ የላንቃ ሰርናዊ (Voiced palatal nasal)	[ɲ]	<ny>
/ʔ/ ነዛሪ የማንቁርት እግድ (Voiced glottal	[ʔ]	<ʔ>

plosive)		
/x/ ኢነዛሪ የትናጋ ሽሉክሉክ (Voiceless velar fricative)	[x]	<x>
/χ/ ኢነዛሪ የእንጥል ሽሉክሉክ (Voiceless uvular fricative)	[χ]	<xh>
/ ħ/ ኢነዛሪ የጉሮሮ ፍትግ (Voiceless pharyngeal fricative)	[ħ]	< ħ >
/ʕ/ ነዛሪ የጉሮሮ ፍትግ (voiced pharyngeal fricative)	[ʕ]	<ʕ>
/ɓ/ ነዛሪ የከንፈር ፈንጅ (Voiced bilabial implosive)	[ɓ]	<bh>
/ɗ/ ነዛሪ የድድ ፈንጅ (Voiced alveolar implosive)	[ɗ]	<dh>
/ɠ / ነዛሪ የትናጋ ፈንጅ (Voiced velar implosive)	[ɠ]	<q>
/ʛ/ ነዛሪ የእንጥል ፈንጅ (Voiced uvular implosive)	[ʛ]	<qh>

ሠንጠረዠ 3 በአሌ ብቻ የሚገኙ ድምፆች ውክልና

5.2 የተነባቢ ድምፆች ውክልና አጠቃቀም ማብራሪያ

/h/ ኢ-ነዛሪ ማንቁርታዊ ሹልክልክ (the voiceless glottal fricative) እንደሌሎቹ ምልክቶች ሁሉ ራሱን ችሎ ኢ-ነዛሪ ማንቁርታዊ ሹልክልክ (voiceless glottal fricative) /h/ ን እንዲወክል ብቻ ሳይሆን በተጨማሪ ከ /b/ /d/ /q/ ጋር ተጣምሮ ሲመጣ የፈንጅ (implosive) ባህርይን ፣ ከ /s/ ጋር ተጣምሮ ሲመጣ ደግሞ የላንቃዊ ሹልክልክ (palatal fricative) የሆነውን / ʃ/ ን፣ ከ /c/ ጋር ሲጣመር ፍትግ የሆነውን / tʃ /ን እንዲወክል እንዲሁም ከ /x/ በፊት ሲመጣ የ ኢ-ነዛሪ እንጥላዊ ሹልክልክ (Voiceless uvular fricative) / χ/ እንዲወክል ተደርጓል። በተመሳሳይ መንገድ /y/ ብቻውን ሲፃፍ የ/j/ ን ድምጽ፣ ከ/n/ ቀጥሎ ሲፃፍ ደግሞ [ɲ] ን እንዲወክል

ተደርጓል። በእንግሊዘኛ ቋንቋ ውስጥ የማይገኙ ነገር ግን በአሌ የሚገኙ የፈንጂነት ባህርይ ያላቸው እንደ /ጭ/ ፣/ጥ/፣ /ቅ/ እና /ጽ/ ድምፆች በላቲኑ /c/፣ /t/፣ እና /k/ ከላይ በቀኝ በኩል የ/'/ ወይም ጭረት ምልክት እንዲኖራቸው በማድረግ /c'/, /t'/, /k'/, /s'/ ድምፆችን እንዲወክሉ ተደርገዋል።

5.3 የአናባቢ ድምፆች ውክልና

የሚከተሉት ምልክቶች የአሌ አናባቢዎችን ወክለው ተጽፈዋል።

ንጥረ ድምፆች በኢ ፒ ኤ (Phonemes in IPA)	ድምፁ (Phones)	የተወከለው ፊደል (Graphemes)
/i/	[i]	<i>
/e/	[e]	<e>
/a/	[a]	<a>
/o/	[o]	<o>
/u/	[u]	<u>

ሠንጠረዥ 4 የአሌ አናባቢዎች ውክልና

5.4 የአናባቢዎች ርዝመትና የተነባቢዎች ጥብቀት

አሌ 5 አጫጭርና 5 ረዣዥም አናባቢዎች አሉት። አጫጭሮቹ አናባቢዎች እያንዳንዳቸው ረዝመው ሲነበቡ የትርጉም ልዩነት ያመጣሉ።

ምሳሌ

aʃi 'ሄደ'
aʃii 'ይሂድ'
fara 'እየሞተ ነው'
faara 'ይሙት'
gatʃ'e 'አለንጋ'
gaatʃ'e 'ጤፍ'

ከምሳሌዎቹ እንደምንረዳው የአንድ አናባቢ አጥሮ ወይም ረዝሞ መነበብ የትርጉም ለውጥ ያመጣል። ስለዚህ ረዝሞ የሚነበብ አናባቢ ሁለት ሆኖ በመጻፍ አጭር ሆኖ ከሚነበበው አምሳያው መለየቱን ማሳየት አስፈላጊ ሆኖአል።

በተመሳሳይ መንገድ ተናባቢዎቹም ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የትርጉም ለውጥ ያመጣሉ።
ምሳሌ

lale 'ሞልቃቃ (ልጅ)

lalle 'ልብስ'

ለአናባቢዎቹ እንደተጠቀምነው ሳይሆን ጥብቀትን በተመለከተ አንድ ተነባቢ ድምጽ ጠብቆ በሚነበብበት ቦታ ሁሉ በሚጠብቀው ድምጽ አናት ላይ ሁለት ነጥብ በማኖር ለምሳሌ (laÏe) ካልጠበቀው አምሳያው ተነባቢ የተለየ መሆኑን ለማመልከት ተወክሏል።

ከላይ የፈተሽናቸውን የድምፅ ሥርዓት ከለየን በኋላ በሁለቱም ማለትም በኢትዮጵያ እና በላቲን ፊደላት ያካሄድናቸውን ውክልና ለማህበረሰቡ ተወካዮች አቅርበናል ። የማህበረሰቡ ተወካዮችም ለቋንቋቸው ይመቻል ያሉትን የላቲን ፊደላት መርጠዋል።

6. *ሥርዓተ ነጥብ*

የአሌ ቋንቋን ለመፃፍ የተመረጠው የእንግሊዘኛ ቋንቋ ፊደል (የላቲን ፊደል) በመሆኑ አዳዲስ ሥርዓተ ነጥቦች ለመፍጠር መሞከር ተገቢ አይሆንም። ስለዚህ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙ ሥርዓተ ነጥቦችን እንዳሉ በመውሰድ ለአሌ ልንጠቀምባቸው እንችላለን።

ከእነዚህ ሥርዓተ ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎቹ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ናቸው።

1. የዐረፍተ ነገር መግቻ(ማብቂያ) (period). አንድ ዐረፍተ ነገር ጽፈን ስንጨርስ ዐረፍተ ነገሩ ያለቀ መሆኑን ለማሳየት መጨረሻው ላይ ይህንን(.) ነጥብ እናደርጋለን።

ምሳሌ- Gudisa pifesi ipifi.
ጉዲሳ ምሳ በላ።

2. ነጠላ ሰረዝ (comma), ነጠላ ሰረዝ የሚያገለግለው በአንድ አረፍተ ነገር ውስጥ ተመሳሳይ ሀሳቦች ወይም ቃላት ሲዘረዘሩ በመሀላቸው ፋታ እየሰጠን ማነበብ እንዳለብን ለማሳየት ነው።

ምሳሌ- Gudisaba, Nigusieba, kusʔe kumʔe karo menekolingito sa ashe.
ጉዲሳ፣ ንጉሴ፣ ኩሴ ና ኩሜ ወደ ትምህርት ቤት ሄዱ።

3. ድርብ ሰረዝ (semi colon) ; በአንድ አረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኙ ሀረጎችን ወይም አረፍተ ነገር አከል ረጃጅም ሀሳቦችን ለመለየት ስንፈልግ ይህንን ሥርዓተ ነጥብ እንጠቀማለን።

ምሳሌ- Gudisa rafatʔe xaʕi; minte shoħomu; manʔe kolengitosa ashi.
ጉዲሳ ከመኝታው ተነሣ፤ ፊቱን ታጠበ፤ ወደ ትምህርት ቤት ሄደ።

4. የጥያቄ ምልክት (question mark) ? ጥያቄ መጠየቅ በሚያስፈልገን ጊዜ በጥያቄው መጨረሻ ላይ ይህንን ምልክት እናደርጋለን።

1.1.1.1 **ምሳሌ-** **ato pife apifanʔaji?**
ምሳህን ትበላለህ?

5. ትዕምርተ ጥቅስ (quotation) " " የሌላ ሰው ንግግርን እንዳለ ወስደን ስናቀርብ ንግግሩን በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ እናስቀምጣለን።

ምሳሌ- Gudisa yela pajna "manʔe kolingitosa ashinayi"?
ጉዲሳ "ወደ ትምህርት ቤት ትሄዳለህ" ብሎ ጠየቀው።

6. ቃለአጋኖ (exclamation)! በጽሁፋችን ውስጥ አንድን ነገር አድንቀን ወይም በአንድ ነገር በጣም መገረማችንን ለማሳየት ስንፈልግ በቃሉ ወይም በሀረጉ መጨረሻ ላይ የቃለአጋኖ ምልክት እናኖራለን።

ምሳሌ፣ inti ifarayi!
ሞተ እንዴ!

7. ቅንፍ (bracket) () ቀደም ሲል የተጠቀሰውን ሀሳብ ወይም ቃል የበለጠ ግልጽ ለማድረግ የገባ ቃልን ወይም ከዋናው ሀሳብ እኩል ጠቃሚ ያልሆነ ነገር ግን ከተነሳው ሀሳብ ጎን መግባት የሚገባው ቃል ወይም ሀረግ ስንጽፍ በቅንፍ እናስገባዋለን።
ምሳሌ፣ ጉዲሳ (የኩሴ ወንድም) አዲስ አበባ ሄደ።

8. ህዝባር (slash) / ዓመተ ምህረት ሲፃፍ ቀኑን፣ ወሩን እና ዓመተ ምህረቱን ለመለየት ወይም በመደበኛ የደብዳቤ ጽሑፎች ላይ የሚሰጡ የደብዳቤ ቁጥር፣ ቀን… የመሳሰሉትን ለያይቶ ለመጻፍ የህዝባር ምልክት ያገለግላል።
ምሳሌ፣ 22/09/2016

9. ጭረት (-) ድርብ ቃላትን ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ ቃላት የተመሰረቱ ቃላትን ለመጻፍ እንዲሁም በአንድ መስመር ላይ ተጠናቆ ያልተጻፈ ቃል ወደሚቀጥለው መስመር መሻገሩን ለማሳየት እንጠቀምበታለን።

ምሳሌ፣ manʔe-kolingto
ትምህርት-ቤት

10. ወዘተ(…) ተመሳሳይ የሆኑ ቃላትን በሙሉ መዘርዘር በማንፈልግበት ወቅት የተወሰኑትን ብቻ ጽፈን ሌሎቹም በእዚሁ መልክ ይቀጥላሉ ለማለት የምንጠቀምበት ሥርዓተ ነጥብ ነው።

ምሳሌ፣ morinʔa sagumoba, shinangoba, mangoba…alasʔa
እዚህ ገበያ ማር፣ ቅቤ፣ እህል…ይሸጣል።

8. ቀጥሎ ያለው አጠር ያለ ምንባብ ለሙከራ በ አሌ ቋንቋ የተጻፈ ነው።

kedhay kdhanʔati papotonʔe pana yayi tʔe kalo kawadho nati iletʔa aga. longotʔonʔa mango xusindhi gitʔa paħakʔo kodhamadhi tʔa xoʕatitay ki tʔehusindhi kitʔatʔe ilʔeħule dhabe kodhʔamadhi. xusitʔay xaʕati ilʔeħule imʔalale kabani dhikʔatate sabite ħadhiqe piyʔatʔetay ilʔa araramepa hantu dhelʔe salaħki hxafasi pisʔi nagayhotay ʕaketeage.

ትርጉም

በድሮ ዘመን አንድ ባልና ሚስት ገዋዳ ከተማ ላይ አብረው ይኖሩ ነበር። አንድ ወቅት በአካባቢያቸው በተፈጠረ ረብሻ ምክንያት አለመግባባት በመካከላቸው ተፈጠረ። በዚህ ምክንያት ሳይስማሙ ቀሩ። በመጨረሻ ላይ ግን በአካባቢው የሀገር ሽማግሌዎች ጥረት ታርቀው አሁን አራት ልጆችን አድርሰው በሰላም እየኖሩ ይገኛሉ።

9. የአሌ ፊደል ገበታ

የአሌ የፊደል ገበታ የተዘጋጀው የፊደላቱ የድግግሞሽ መጠንን ታሳቢ በማድረግ ነው።

a	i	o	n	k
t	e	u	y	s
p	r	l	g	m
dh	h	qh	sh	x
d	b	q	hx	w
f	ħ	z	ʔ	c’
bh	t’	k’	s’	ch
ʕ	ny			

ሠንጠረዠ 5 የአሌ ፊደል ገበታ

10. የአሌ ቋንቋ ድምፆች ውክልና በላቲን

Orthographic Representation Of sounds of Ale in Latin script

የአይፒኤ ምልክቶች (IPA <u>Symbol)</u>	የተወከሉ ፊደላት (Graphemes)
b	<b>
p	<p>
ɓ	<bh>
t	<t>
ɗ	<dh>
tʼ	<tʼ>
tʃ	<c’>
g	<g>
k	<k>
ɠ	<q>
kʼ	<k’>
ʛ	<qh>
ʔ	<ʔ>
f	<f>
s	<s>
s’	<s’>
ʃ	<sh>
x	<x>
d	<d>
χ	<xh>
ħ	<ħ>
z	<z>
h	<h>
ʕ	<ʕ>
tʃ	<ch>
m	<m>
n	<n>
ɲ	<ny>
l	<l>
r	<r>
w	<w>

j	<y>

ሠንጠረዠ 6 የአሌ ቋንቋ ድምፆች ውክልና በላቲን

II. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በደቡብ ኢትዮጵያ የሚነገረው እና የኩሺቲክ ቋንቋ ቤተሰብ አባል የሆነው የአሌ ቋንቋ የድምጽ ስርዓት (Phonetic and Phonology) በጥልቀት መርምሮ ፣ ለቋንቋው ተስማሚ የሆነ ሥርዓተ ጽሕፈት (Orthography) መቅረጽ ላይ ያነጣጠረ ነው ። ጥናቱ በአሌ ቋንቋ ውስጥ (32) ተነባቢ ድምፆች እና (5) አናባቢ ድምፆች መኖራቸውን ለይቷል። እንዲሁም፣ የተነባቢ ድምፆች መጥበቅ/መላላት (gemination) እና የአናባቢ ድምፆች መርዘም/ማጠር (length) የትርጉም ልዩነት እንደሚያመጡ ተረጋግጧል።

የተለዩትን የንግግር ድምፆች መሠረት በማድረግ ለቋንቋው የሚሆን የፊደል ገበታ እና የሥርዓተ ነጥቦች ውክልና ተዘጋጅቶ፣ በተዘጋጀው ሥርዓተ ጽሕፈት አጠር ያለ ምንባብ ለሙከራ ቀርቧል። የመስክ መረጃ አሰባሰቡ በቃለ ምልልስ፣ በጽሑፍ መጠይቅ፣ በስዋዴሽ 400 የቃላት ዝርዝር እና ሚኒማል ፔሮችን በመጠቀም በአሌ ዞን በአካል ተገኝቶ በጥንቃቄ ተከናውኗል። መረጃውም የፎነቲክና ፎኖሎጂ አሐዶችን በመለየት እና የአጻጻፍ መርሆችን በመመርመር ተንትኗል ።

በዚህ ትንተና ውጤት ተግባራዊ፣ ቀልጣፋና ተጠቃሚዎች የሚቀበሉት ሥርዓተ ጽሕፈት ተዘጋጅቶ ለማኅበረሰቡ ቀርቧል። በመጨረሻም፣ ተመራማሪዎቹ ይህ ጥናት የአሌ ቋንቋን የድምጽ ቆጠራ ሙሉ በሙሉ በመመርመርና በመመዝገብ እንዲሁም የመጀመሪያውን ሳይንሳዊ ሥርዓተ ጽሕፈት በመፍጠር ረገድ ታሪካዊ አስተዋጽኦ እንዳበረከተ ያምናሉ ። ይህም ጥናት ለቋንቋ ሊቃውንት፣ ለተማሪዎች፣ ለአሌ ሕዝብ ትምህርትና ሥነ ጽሑፍ እንዲሁም ለቀጣይ ምርምሮች ጠቃሚ መሠረት ይሆናል ተብሎ ይታሰባል።

ዋቢ መጽሐፎች

Assefa, D. (2010). *The phonology of Gawwada* [Unpublished master's thesis]. Addis Ababa University.

Bender, M. L. (1971). *The languages of Ethiopia: A new lexicostatistic classification and some problems of diffusion*. Anthropological Linguistics, 13(5), 165–288.

Bender, M. L. (1976). *Language in Ethiopia*. Oxford University Press.

Black, Paul. (1976). Werizoid. In M. L. Bender et.al (eds), *The non-Semitic Language of Ethiopia,* Carbondal, 222-231.

Bowern, C. (2015). *Linguistic fieldwork: A practical guide* (2nd ed.). Palgrave Macmillan.

Cahill, M., & Karan, E. (2008). *Factors in designing effective orthographies for unwritten languages*. SIL International.

Crystal, D. (2008). *A dictionary of linguistics and phonetics* (6th ed.). Blackwell Publishing.

Firew Girma. (2011). *The syllable structure and syllable-based morphophonemic processes in Gawwada: Based on moraic model representations* (Master's thesis, Addis Ababa University).

Geberew Tulu. (2003). The morphology of Gewada Unpublished MA Thesis: Addis Ababa University.

Hagège, C. (2003). *[Linguistic typology / phonological description work cited in relation to Gawwada]*.

Haregewoin Kebede. (2003). Aspects of Phonology of Gawwada. In Zena lisan *Journal of Ethiopian Languages Research Center*. Vol.3, Artistic printers Addis Ababa. pp42-56.

Haregewoin Kebede. (2011). Computerized Ale (Gawwada)- Amharic English Dictionary Unpublished MA Thesis: Addis Ababa University.

Hayes, B. (1989). Compensatory lengthening in moraic phonology. *Linguistic Inquiry, 20*(2), 253–306.

Horsch, Roland. (2006). Suggesting Orthography for the Dullay Language Cluster: 3rd.

Hyman, L. M. (1975). *Phonology: Theory and analysis*. Holt, Rinehart and Winston.

Swadesh, M. (1955). *Towards greater accuracy in lexicostatistic dating*. International Journal of American Linguistics, 21(2), 121–137.

Tosco, M. (2009). Loanwords in Gawwada, a Cushitic language of Ethiopia. In M. Haspelmath & U. Tadmor (Eds.), *Loanwords in the world's languages: A comparative handbook* (pp. 124–141). De Gruyter Mouton.